# መርዝን ነው በመርዙ መርዝ አርጎ መመረዝ

(ሄኖክ የሺጥላ)

መርዝን በመርዝነት እንደመርዝ ለመመረዝ...
መርዝን ነው በመርዙ...መርዝ አርጎ ማስመረዝ::
አሲድን በአሲድ....
አጥንቱ እስኪረግፍ....ብን እስኪል እንዳ'መድ
መጠቃት መቆጨት..ሆኖን.....የሚያቃጥል የሚያነፈር እሳት....
መርጨት ነው ማቃጠል: እንዲነፍር ጠላት::
መግፋት ነው መ-"መለሰ" ወደበቀለበት.....
ከትብቱ ማስታረቅ...ከደደቢት መሬት::
በመርዝ ነው መርዝን መርዞ ማስመረዝ....
ባመጽ በ-እምቢታ ነው...አጥንቱን መመዝመዝ::
መርዝን ነው መርዝ አርጎ....በጥብጦ መመረዝ....
ጨቅጭቆ ነው ፈጭቶ....ወባውን መፈውስ....
ጠፍጥፎ ነው ጋግሮ...ህቅ እስኪለው.... ማጉረስ::
መርዝን ነው በመርዙ....መርዝ አርጎ መመረዝ....
መጋኛ ነው...እጀሰብ....የሚጥል በሽታ.....
ወፍ ነው...ቡዳ....አዙሪት....ከተሰጠው ፋታ....
ሃገር ለሚነግድ....ለታሪክ...አዙሪት....
ለኩሶ ማሽተት ነው....የነጻነት ክብሪት::
መርዝን ነው በመርዙ መርዝ አርጎ ማንገብገብ
በራሱ...እሳት ነው.....ጆርባውን መለብለብ::
እንጂ እያስተዋሉ መርዝን ቢያወድሱት...
መርዝን ቢያሞግሱት......
እየተላ ይሄዳል....እየሆመጠጠ.....
ተባይ እየሳበ....ሽበት እያማጠ::
ከድንጋይ ተስቦ ከድንጋይ የወጣ....
ይህ ጥቁር እባብ ነው....ችንካር ነው ማጎጣ::
መርዝ ነው...መርዛማ.....
መልኩን አመሳስሎ ታሪክ የሚቀብር....ወገን የሚያደማ::
እሱን በመርዝ ነው....መርዝ አርጎ መመረዝ....
እሱን ነው በአሲድ...አጥንቱን መመዝመዝ::

እሱን ነው....ጠፍሮ....ከወህኒ ቤት ማጎር....
እሱን ነው ነስንሶ..ቆዳውን ማኾርጎርጎር::
የመርዝ አይኑ ይቅላ....እሱ መግል ያውጣ
መርዝ ነው ይንተክተክ.....ተቃጥሎ እንቅልፍ ይጣ....
መርዝን በመርዝነት....መርዞ..መመረዝ....
መርዝ እየመረዙ....በመርዝ ነው ማድረቅ...
በመርዝ ነው... ማጥዘዝ
በመርዝ ነው ማፌስ::
መርዝማ...ለመርዙ ነበር ለመርዛማው....
ገድሎ ለሚያቃብር...አብሮ ለሚያነባው...::
ወንድ ከሆኑማ....መርዝን ለወያኔ.....
ጅግና ከሆኑማ እሱ ነበር ወኔ...::
ሚስትን ቢያቃጥሉ....
ሃገርን ቢለቁ.....
ተሰደው ቢጠፉ....ጫካ ቢደበቁ.....
አሻራ የለውም....
ክፉ ጨካን እንጂ....ቆራጥ አንለውም....::
ወንድ ከሆንማ....
አሲድ....ለታገሰ.....
አጥቦ ላለበሰ....
አቅፎ ላጎረሰ.....
ሰው እንዴት ለሚስቱ....
ለፍቅር እህቱ.....
ዛሬ መች ወንድ አለ....ውንድም የት-አባቱ...::
ወንድማ ተራራ ገመገም ይወጣል....
ወንድ እምቢኝ ነው ስሙ....
በቃኝ... እንጂ አሽሙር...መቼ ካፉ ይወጣል...::
ወንድ የሳት ሰደድ ነው....ክንዱ የሚያቃጥል....
ወንድ...የቁርጥ ቀን ነው....ሰው ሲከዳ 'እማይጥል....::
ወንድ ቆፍጣና ነው....ግንባሩ 'ሚያወራ....
ወንድ....ሲሸልል ነው....ሲያቅራራ...'እሚያስፈራ...::
ወንድ መቼ ሆነና....አሲድ የሚደፋ
ፍቅር ነው...ለሚስቱ....ፍቅር ነው ለናቱ
ፍቅር ነው ላገሩ.....ነብሱን የሚያጠፋ...::

ዛሬ ግን ወንዶቹ....እጅጉን ሰልጥነው.....
መረገጥ ፍቅር ሆኖ.....ባርነትን ለምደው....
ነገር ተቀያይሮ ኩነት ተገላብጦ....
ሚስቱን እየላጠ....ባቃጣይ ይዳኛል.....
ወንድነት ሲጨምት.....ከማጀት ይገኛል::
ወንድ ከሆኑማ......መች ጠፍቶ...አሲድ መርጫ
ወንድማ ከሆኑ....አለ ነጻ መውጫ::....
ይህንን ድፍረትህን ምናለ....ብትይዘው....
ሀገርህ ተጭንቃ.....ሚስትህ ላይ ታፈሰው?.....
ምናል ወንድነትክን....ለሌላ ባዋልከው....
አንተም እንደ-ቴዎድሮስ ዝንተ አለም....በነገስክ....ሁሌ በታወስከው::